# ለዋሽንግተኑ የዕለት ረሀብተኛ

ዝክረነገር (ከአሜሪካ)

ይህ ጠጉረ ልውጥ ሰው የፈረንጅ ቀናጣ
ምነው ባዛኙቱ ጉድ ይዞብን መጣ::
የዋህ ሰው ልበለው ወይስ ያው ፈረንጅ
ለእኛ ሲል ሰቆቃ በረሀብ ሲዋጅ::

አብዬ መለስ ይህንን ቢሰሙ
አገር ጉባይ ብለው ሱባይ ይገባሉ፣
ፈረንጅ አያስፈታህ ብለው ተናግረዋል
ድፍን ዋሽንግተን ምነው ይዘነጋል::

እንደእንቧይ የሚፈረጥ የመሰለው ገላ
እንዴት ባልበላ አንጀት በጠሀይ ይጉላላ
አስመሳዩ እያለ የዕንቅቡ ይቁላላ?

ነጭ መቼም ነጭ ነው አይራብ በከንቱ
የነገን ስም ክብረት ሰሎ ባንደበቱ
አበጀህ ተባለ ገና በመክሊቱ::

ጆብዱ ሠራሁ ብሎ አሽቶ መናገር
ብላት ነው ይባላል በድፍን አገር::
ያፍታ ረሀብ አስበው ብዙ ያወራሉ
ለሰው ለንሰሀ እንደተሰቀሉ
ገደል ይዘላሉ ከፎቅ ይወርዳሉ
በደመ ነፍሳቸው ብራቮ እንዲባሉ
ሆድ ሲያውቅ ክትፎ ማታ እየተባባሉ::

ጥማትን ለምናወቅ ጠኔውን ለኖርነው
የወኪል ረሀብ ይቅርብን ምፀት ነው
ዝቅ ሲል ርግማን ያለየም ሀጢያት ነው::

በዋሽንግተኑ በሠላሰው ታቦት በሰላው ደብር፣
በኢሠፓ ማርያም፣ በነውጠኛ  አድባር፣
ይኸው ግዝት ይሁን ፈረንጅ አይራብ፣ ነጭ አይቸገር::